# ማሕበር ተጋሩ ሰሜን ኣሜሪካ (ማ.ተ.ሰ.ኣ)

# UNION OF TIGREANS IN NORTH AMERICA (UTNA)

P.O.BOX 73736
Washington, DC 20056
utnaoffice@gmail.com

Tel. (202) 862-4367
Fax. (202) 265-8703
www.utna.org

ቀን፡ ዲሰምበር 14፣ 2019

ዋሽንግተን ዲሲ

## በወቅታዊ ጉዳይ ከትግራይ ተወላጆች ማሕበር በሰሜን አሜሪካ የተላለፈ መልዕክት

በትግራይ መንግስት ፕሬዝዳንት ዶ/ር ደብረጽዮን ገብረሚካኤል ላይ የተሰራጨው ሐሰተኛ እና አስነዋሪ መረጃ "ሐሰተኛ ዜና" ብቻ ተብሎ ሊታለፍ የማይገባ ይልቁንስ ትግራይን ለማዳከም እና የትግራይን ህዝብ ለመበታተን እየተጎነጎነ ካለው ሴራ አካል እንደኾነ ማሕበራችን በሚገባ ይረዳል።
ሐሳብን በነጻ ለመግለጽ እና የሚዲያ ነጻነትን እውን እንዲኾን ህይወት የከፈለው የትግራይ ህዝብ በአጎናጸፈው መብት ተጠቅመው ጸረ ትግራይ መረጃዎችን በመልቀቅ ከተሰማሩት ሚዲያዎች ዋልታ ቴሌቪዥን አንዱ መኾኑ ከተረዳን ውለን አድረናል። ለሀገራዊ መግባባት ሲባል ስንከፍለው የቆየን መስዋዕትነት አኩሪ ቢኾንም ትዕግስትም ወሰን አለው።

ማሕበራችን ዋልታ ኢንፎርሜሽን ማእከል ያሰራጨውን እኩይ ሐሰተኛ "ዜና" በጽኑ ያወግዛል። ለኢትዮጵያ ቀጣይነት እንቆረቆራለን የሚሉ ወገኖች ተመሳሳይ አቋም በመያዝ በቋፍ ላይ ያለውን የሀገሪቱን ሁኔታ በመረዳት በዋልታ እና መሰል በጥላቻ የታወሩ ሚድያዎች ላይ 'በቃ' እንዲሉ ጥሪ እናቀርባለን።

የጸረ ትግራይ ሀይሎች ትግራይን የማዳከም ህልም እንደ ጉም የሚበን ቅዠት ነው።

ድል ለትግራይ ህዝብ!

ማሕበር ተጋሩ ሰሜን ኣሜሪካ
ማእኸላይ ቤት ጽሕፈት
ዋሽንግተን ዲሲ